# የነቢ ዒሳ መልእክት

ጊርሃርድ ኔልስ

የሕይወት በር
የመ.ሣ.ቁ. 4937
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

# የነቢ ዒሳ መልእክት

ሙስሊሞች ሁሉ ነቢ ዒሳን በአክብሮት ከፍ አድርገው ይመለከቱታል። እርሱም መልእክተኛው ኢየሱስ ነው። እንደሚታወቀው የአንድ መልእክተኛ ዕቅድና ዓላማ መልእክት ማስተላለፍ ነው። ነቢ ዒሳ ለእኛ ያመጣው መልእክት ምንድነው? ይህ መልእክት በቁርዓን ውስጥ አልተመዘገበም። ኢየሱስ የኖረው ቁርዓን ከመጻፉ ከ600 ዓመታት በፊት ስለነበር፥ ይህ ለመረዳት የሚያስቸግር አይሆንም። ዛሬ ብዙ ሙስሊም መምህራን ይህ መልእክት ለአይሁዶች ብቻ ተሰጥቶ ሳለ እንደጠፋ አድርገው ያስተምራሉ። ይህ ቁርዓን የሚያስተምረውን የሚቃረን ስለሆነ፥ እንዲህ ማድረግ አልነበረባቸውም።

ቁርዓን፥ «በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርዓን)፥ ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማዒልና ወደ ኢስሐቅም፥ ወደ ያዕቆብና ወደ ነገዶቹም፥ በተወረደው፥ በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት፥ በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንሆን አመንን» (ሱረቱ 2፡136) በማለት በግልጽ ያስቀምጣል።

ሙስሊሞች በዚህ ማጠናከርያ መሠረት ለአብርሃም፥ ለሙሴና ለኢየሱስ በተሰጠው ራእይ፥ ያምናሉን? ኢማኑን በማናዘዝ፥ «በተገለጹት መጻሕፍትና በነቢያት (በመልእክተኞች) ሁሉ እናምናለን» ማለት ቀላል ነው፤ በተግባር ሲታይ ግን እንዲህ አልሆነም! የአብርሃምን የሙሴንና፥ የኢየሱስን መልእክት የያዘው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃልነቱ አክትሟል ይላሉ የሙስሊም መምህራን። በተደጋጋሚ ተቀያይሯል። ስለዚህም ነው ቁርዓን መገለጽ የነበረበት።

«ወደ አንተም ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን፥ እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ» (ሱረቱ 10፡94)። መጽሐፉ የትኛው ነው? ከቁርዓን በፊት የተሰጠው መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ ከሌለ፥ የመጽሐፉ ሰዎች እንዴት ያነቡታል? ወይስ ቁርዓን የተበላሸ መጽሐፍ እንዲያነቡ ያሳስባቸው ይሆን? በአንጻሩ ቁርዓን፥ «የማታውቁም ብትሆኑ፥ የመጽሐፉን ባለቤቶች ጠይቁ» (ሱረቱ 21፡7) ይላል። እርሱም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይህን ትምህርት የሚቃረኑትን ሰዎች ለማመን ይቻል ይሆን?

መልካም፤ አሁን ወደ ኢየሱስ መልእክት እንመለስ። ይህም የሚገኘው በወንጌል ውስጥ ነው። ሙስሊምም፥ እንደማንኛውም ሰው አማኝ ለመሆን ይህንን መቀበል አለበት። እንዲሁም «የአላህንም ንግግሮች ለዋጭ የለም» (ሱረቱ 6፡34)።

ቀጥለን የኢየሱስ መልእክት ምን እንደሆነ እንመለከታለን፡-

## ነቢ ዒሳ ስለ ራሱ ምን አለ?

መልእክቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ሲሆን፥ እውነትነቱም ሊፈተን የሚችል ነው።

> «ትምህርቱስ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም፤ ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር፥ እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል»
>
> (ዮሐንስ 7፡16)

መልእክቱ ዘላለማዊና የማይለወጥ ነው።

> «ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን አያልፍም»
> (ማቴዎስ 24፡35)

እርሱ በዓለም ውስጥ አልነበረም፤ ዳሩ ግን ወደ ዓለም መጣ።

> «እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል»
>
> (ዮሐንስ 18፡37)

እርሱ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቷል።

> «ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፤
> እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው»
> (ዮሐንስ 3፡13)

ይህ የእግዚአብሔር እውነት ስለሆነ እርሱ ያለውን ማመኑ የሰው ኃላፊነት ነው።

> «ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማነው? እውነት የምናገር ከሆንሁ፥
> እናንተ ስለምን አታምኑኝም?»
>
> (ዮሐንስ 8፡46)

እግዚአብሔር ሁልጊዜም ከኢየሱስ ጋር ነበር።

> «የላከኝም ከእኔ ጋር ነው፤ እኔ ደስ የሚያሰኘውን ዘወትር አደርጋለሁና አብ ብቻዬን አይተወኝም»
>
> (ዮሐንስ 8፡29)

የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት ማለት በመጀመሪያ ደረጃ ኢየሱስን ማመን ነው እንጂ የተለያዩ ሥርዓቶች ለመፈጸም ደፋ ቀና ማለት አይደለም፥

«ይህ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው»
(ዮሐንስ 6፡29)

በኢየሱስ አስተሳሰብ አንድ ቁም ነገር ብቻ ነበር። ይህም አባቱን ደስ ማሰኘትና ሥራውን መፈጸም ነው።

«የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ፥ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው»
(ዮሐንስ 4፡34)

ኢየሱስ ስለ ማንነቱ የሚናገረውንና የሆነውን ወደ ጎን መተው ማለት፥ ራሱ እግዚአብሔርን ማግለል ማለት ነው!

«እኔንም የጣለ የላከኝን ይጥላል»
(ሉቃስ 10፡16)

እርሱ የመጣው መልእክት ለማድረስ ብቻ ሳይሆን፥ ሥራውንም ለመፈጸም ነው።

«የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና»
(ሉቃስ 19፡10)

ከሰብዓዊ አዕምሮ ግምት ተጻራሪ በሆነ መልኩ ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ ለመጥራትና ከሲዖል ጫፍ ለማትረፍ መጣ። በመሆኑም ኃጢአት ላልነካቸው ሰዎች አያስፈልጋቸውም። ለመሆኑ ኃጢአት ያልነካው ሰው አለን? እኛስ ኃጢአት የሌለብን ነን?

«ሕመምተኞች እንጂ ብርቱዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም፤ ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም»
(ማርቆስ 2፡17)

ለደካማው ድካሙን እንደሚያቃልል ወንድም ሆኖ ቀረበ። ለታወከው ልባችን ሰላምን ለማጎናጸፍ ይሻል።

«እናንተ ደካሞች፥ ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ የዋህ፥ በልቤም ትሑት ነኝና ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ፥ ሸክሜም ቀሊል ነውና»
(ማቴዎስ 11፡28-30)

ውኃ ለሕይወት አስፈላጊ ነው። በመንፈሳዊ አነጋገርም ኢየሱስ የዘላለምን ሕይወት ለማግኘትና ለማቆየት «ውኃ»ውን ይሰጠናል ማለት ነው።

> «ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን፥ መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል»
>
> (ዮሐንስ 7፡37)

> «ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ እንደገና ይጠማል፤ እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፤ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ»
>
> (ዮሐንስ 4፡13-14)

እንግዲህ የኢየሱስ መልእክት ታማኝነት እንዳለው እንዴት እናውቃለን? ኢየሱስ እንዲህ ይላል፡- የምሠራውን ሥራ (ተአምራት) ተመልከቱ፤ እንዲሁም ቅዱሳት መጻሕፍትን (ታውራትን) መርምሩ፤ ምክንያቱም እነዚህ እኔን በተመለከተ ባሉአቸው በርካታ ትንቢቶች ስለ እኔ ይመሰክራሉና።

> «አብ ልፈጽመው የሰጠኝ ሥራ፥ ይህ የማደርገው ሥራ አብ እንደላከኝ ስለ እኔ ይመሰክራልና። የላከኝ አብም እርሱ ስለ እኔ መስክሮአል። ድምፁን ከቶ አልሰማችሁም፤ መልኩንም አላያችሁም፤ እርሱም የላከውን እናንተ አታምኑምና፥ በእናንተ ዘንድ የሚኖር ቃሉ የላችሁም። እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና፥ እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፤ ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም። ከሰው ክብርን አልቀበልም፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ፍቅር በራሳችሁ እንደሌላችሁ አውቃችኋል። እኔ በአባቴ ስም መጥቻለሁ፤ አልተቀበላችሁኝም፤ ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ እርሱን ትቀበሉታላችሁ»
>
> (ዮሐንስ 5፡36-43)

ስለ ራሱ እንደ ሦስተኛ ሰው እየተናገረ ኢየሱስ ታላቅ እውነትን ይገልጻል። በዚህ እውነት የማይኖር ማንም ቢሆን ከፉና ከብርሃን የሚሸሽ የጥፋት ሰው ነው።

> «በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል። ብርሃንም ወደ ዓለም ስለመጣ፥ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለወደዱ ፍርዱ ይህ ነው። ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፥ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም፤ እውነትን የሚያደርግ ግን ሥራው በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደሆነ ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል»
>
> (ዮሐንስ 3፡18-21)

ይህንንም ስለ ራሱ የበለጠ በማብራራት የበለጠ ያጎላዋል፡-

«እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ፥ በጨለማ አይመላለስም»

(ዮሐንስ 8፡12)

የመምጣቱ ዐቢይ ምክንያት «ሕይወት እንዲሆንልን፥ እንዲበዛልንም» ነው። ለዚሁም ዐቢይ ምክንያት ሕይወቱን ሠውቷል።

«ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ»

(ዮሐንስ 10፡10)

«መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል»

(ዮሐንስ 10፡11)

«መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ አብም እንደሚያውቀኝ፥ እኔም አብን እንደማውቀው፥ የራሴን በጎች አውቃለሁ፤ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤
ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ»

(ዮሐንስ 10፡14-15)

ይህ ነፍሱን የ «ማኖሩ» ጉዳይ በራሱ ሥልጣን፥ ያለምንም አስገዳጅ ኃይል፥ በፈቃደኝነት የፈጸመው ሥራ ነው።

«ነፍሴን አነሣት ዘንድ አኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል። እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ፥ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ፤ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ»

(ዮሐንስ 10፡17-18)

ኢየሱስ ሊሰጠን የመጣው ይህ «የሚበዛልን ሕይወት» በውስጡ የዘላለም ሕይወትን ዋስትናም አካቶ ይዟል። እግዚአብሔር አብና ወልድ አንድ ስለሆኑ፥ ይኸንን ሊያደርግ ይችላል!

«በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔም አውቃቸዋለሁ፤ ይከተሉኝማል፤ እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፤ ለዘላለምም አይጠፉም፤ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም። የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፤ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም። እኔና አብ አንድ ነን»

(ዮሐንስ 10፡27-30)

ይህ አንድ ጊዜ ብቻ የተነገረና ምናልባትም በተሳሳተ መንገድ የተተረጎመ አይደለም። ኢየሱስ ለሦስት ቀናት ከሙታን መካከል የሰነበተውን ወንድሟን ወደ ሕይወት ለመለሰላት ግለሰብም የሚከተለውን ተናግሯል፡-

«ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤ ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፤ ይህን ታምኚያለሽን? »

(ዮሐንስ 11፡25-26)

እዚህ ላይ ኢየሱስ በመንፈሳዊና በሥጋዊ ሞት መካከል ገደብ አብጅቷል። የኋለኛው ሞት የሕልውና መክሰም ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ወደ ገሃነም መግባት ነው። በኢየሱስ ማመን ማለት ደግሞ በእግዚአብሔር ላይ እምነት መጣል ማለት ነው።

> «በእኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ ነው እንጂ በእኔ አይደለም፤ እኔንም የሚያይ የላከኝን ያያል። በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ»
>
> (ዮሐንስ 12፡44-46)

በእርግጥ ኢየሱስ ከኩነኔ ነፃ ሆኖ ወደ ዘላለም ደኅንነት ለመሄድ ብቸኛው መንገድ እርሱ እንደሆነ በማያሻሙ ቃላት ገልጿል።

> «እኔ መንገድና እውነት፥ ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር»
>
> (ዮሐንስ 14፡6-7)

ይህም ደግሞ ከሚከተለው ዐረፍተ ነገር ይበልጥ ጉልህ ሆኗል፡-

> «ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም፤ ከወልድም በቀር ወልድም ሊገልጥለት ከሚወድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም»።

ኢየሱስ ራሱን በብዙ መንገዶች ገልጿል። ከእነዚህም የአገላለጽ መንገዶች አንዱ በተለይ በጣም አድርጎ የሚነካ ነው። በዚህም ከየት እንደመጣና ሥራውንም ይገልጻል።

> «የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና»
>
> (ዮሐንስ 6፡33)

> «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፤ በእኔ የሚያምን ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም»
>
> (ዮሐንስ 6፡35)

> «ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም፤ ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና። ከሰጠኝም ሁሉ አንድን ስንኳ እንዳላጠፋ፥ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው እንጂ የላከኝ አብ ፈቃድ ይህ ነው»
>
> (ዮሐንስ 6፡37-39)

እዚህ ላይ ኢየሱስ ስለ ሌሎች ሰዎች ወይም ነቢያት እንዲሁ

አጠቃላይ የሆኑ ዐረፍተ ነገሮችን እየተጠቀመ አለመሆኑ ግልጽ ነው።

> «አብን ያየ ማንም የለም፤ ከእግዚአብሔር ከሆነ በቀር፥ እርሱ አብን አይቶአል። እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው። የሕይወት

እንጀራ እኔ ነኝ»

(ዮሐንስ 6፡46-48)

«ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፤ እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው፤ ሕይወትም ነው»

(ዮሐንስ 6፡63)

ሁልጊዜም ኢየሱስ ግልጽና ቀጥተኛ ነው፡-

«እግዚአብሔርስ አባታችሁ ከሆነ በወደዳችሁኝ ነበር፤ እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፤ እርሱ ላከኝ እንጂ፥ ከራሴ አልመጣሁምና»

(ዮሐንስ 8፡42)።

ኢየሱስን ከነቢያት እንደ አንዱ አድርጎ መቀበል ብቻም በቂ አይደለም።

«እናንተ ከታች ናችሁ፤ እኔ ከላይ ነኝ፤ እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ፤ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም። እንግዲህ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ አልኋችሁ፤ እኔ እንደሆንሁ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁና»

(ዮሐንስ 8፡23-24)

በዕብራይስጥ «እኔ ነኝ» የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ስም ከሆነው ከ «ጂሆቫ» ጋር አንድ እንደሆነ ልብ ማለት ያሻል። አይሁዳውያን እርሱን ለመግደል የፈለጉት በዚህ ምክንያት ነው። ኢየሱስ ከመሞቱ ቀደም ብሎ የቅርብ ተከታዮቹን በመውሰድ ምሥጢሩን ገለጸላቸው።

«ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ደግሞ ዓለምን እተዋለሁ፤ ወደ አብም እሄዳለሁ»

(ዮሐንስ 16፡28)

ተከታዮቹ መለኮታዊነቱን እንዲያምኑ ገፋፍቷቸዋል አባባሉንም አጠናክሮታል። «እኔን ያየ አብን አይቶአል»።

«እኔ በአብ እንዳለሁ፥ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፤ ባይሆንስ ስለ ራሱ ስለ ሥራው እመኑኝ»

(ዮሐንስ 14፡9-11)

በአንድ በተመዘገበው ጸሎቱ ላይ ኢየሱስ ከአባቱ ጋር በመሆን፥ ከመወለዱ አስቀድሞ ስለነበረው ሕልውና ይጠቅሳል። ዋሽቶ ይሆን?

«አሁንም፥ አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ»

(ዮሐንስ 17፡5)

ኢየሱስ ከሰብዓዊ እናት ስለተወለደ፥ እውነተኛ ሰብዓዊ አካል ነበረው። በመሆኑም ተርቧል፤ ደክሟል፤ ጸልዮአል፤ አዝኗል፤ እንዲሁም ተሰቃይቷል። በሌላ በኩልም ያለ ሥጋዊ አባት ከእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ስለተወለደ መለኮታዊ ነበር።

ስለሆነም መፈወስ፥ ሙታንን ማስነሣት፥ በውኃ ላይ መራመድ፥ ኃጢአትን ማስተሰረይ፥ ማዕበሉን ጸጥ ማድረግና ሌሎች በርካታ የተዘገቡ ተአምራቶች መፈጸም ችሏል። በዚህም መጀመሪያ ስንሰማው የሚያስደነግጠንን ማዕረግ ሊጎናጸፍ በቅቷል።

«ሁላቸውም፥ እንግዲያስ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህን? አሉት። እርሱም:- እኔ እንደሆንሁ እናንተ ትላላችሁ አላቸው»

(ሉቃስ 22:70)

የሞትን ጨምሮ ከማንኛውም ዓይነት ፍርሃት፥ ከሰይጣናዊ ተጽዕኖዎችና ከኃጢአት ነፃ መውጣት የሚቻለው በእርሱ ብቻ ነው።

«እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ፥ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ»
(ዮሐንስ 8:36)

አንድ ጊዜ ኢየሱስ ስለ ራሱ እንግዳ የሆነ መግለጫ ሰጠ። ምን ማለቱ እንደሆነ ይገባን ይሆን?

«እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ አብርሃም ሳይወለድ እኔ ነኝ»
(ዮሐንስ 8:58)

«እኔ ነኝ» ማለት እግዚአብሔር ማለት እንደሆነ አንዘነጋም። እዚህ ላይ ተጨማሪ መልእክት ይስተዋላል። እግዚአብሔር ዘላለማዊ ስለሆነ፥ ለእርሱ «ነበር» ወይም «ይሆናል» የሚሉ አገላለጾች ፋይዳ የላቸውም። ሁልጊዜም እርሱ በአሁን የጊዜ ግሥ ይገለጻል። እዚህ ላይም ለማለት የፈለገው «አብርሃም ከመወለዱ በፊት እኔ ለዘላለም ሕያው ነበርኩ» ነው። ይህም ሆኖ በሰማየ ሰማያት ከእኛ ገለል ብሎ የሚኖር አይደለም። እንተንና እኔን ይወደናል! ምላሽ እንድንሰጠውም ይፈልጋል።

«አብ እንደወደደኝ፥ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ»
(ዮሐንስ 15:9)

ፍቅሩም የወሬ ፍቅር ሳይሆን፥ በመስቀል ላይ የተረጋገጠ ነው!

«ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም»
(ዮሐንስ 15:13)

ምናልባትም በኢየሱስ ላይ ጥላቻ አይኖረን ይሆናል። ነገር ግን እርሱን ወደ ሰብአዊ ደረጃ ዝቅ በማድረግ እናዋርደዋለን፤ ወይም ስለ እርሱ ግድ የለንም። እርሱ የተናገረውን ልብ በል:-

«እኔን የሚጠላ አባቴን ደግሞ ይጠላል»
(ዮሐንስ 15:23)

ኢየሱስ እየቀረበ ስለመጣው ሞቱና ስለዚሁም ሞት ዓላማ ብዙ ጊዜ ተናግሮ ነበር።

«የሰው ልጅ ሊያገለግል፥ ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ
እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም»

(ማቴዎስ 20፡28)

ቤዛ የሚለው ቃል ዛሬ እምብዛም ከአገልግሎት ላይ አይውልም። አንዳንድ ጊዜ የጠለፋ ወንጀለኞች ቤዛ እንደሚጠይቁ እናነባለን። ይህም ቤዛ ታጋጆቹን ነፃ ለማውጣት የሚከፈል ዋጋ ነው። ኢየሱስም እኛን ከኃጢአት ኩነኔ ሊያወጣን ዋጋ ከፍሎልናል።

ኢየሱስ ለቅርብ ተከታዮቹ አራት ጊዜ ስለ ሞቱ አስቀድሞ ነግሯቸዋል። ሆኖም እነርሱ እንኳ በመጀመሪያ ይህንን መረዳት አስቸጋሪ ሆኖባቸዋል። እኛም ደግሞ እርሱ ማን እንደሆነና ምንስ እንዳደረገልን ለመረዳት ይቸግረን ይሆናል። ሰው የእግዚአብሔርን ነገር ሙሉ ለሙሉ ከቶ መረዳት ይችል ይሆን?

«ደቀ መዛሙርቱንም ያስተምር ስለነበር ማንም ያውቅ ዘንድ አልወደደም፤ ለእነርሱም፡- የሰው ልጅ በሰዎች እጅ አልፎ ይሰጣል› ይገድሉትማል፤ ተገድሎም በሦስተኛው ቀን ይነሣል፤ ይላቸው ነበር»

(ማርቆስ 9፡31)

«እነሆ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፤ የሰው ልጅም ለካህናት አለቆችና ለጻፎች አልፎ ይሰጣል፤ የሞት ፍርድም ይፈርዱበታል፤ ለአሕዛብም አሳልፈው ይሰጡታል፤ ይዘብቱበትማል፤ ይተፉበትማል፤ ይገርፉትማል፤ ይገድሉትማል፤ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል»

(ማርቆስ 10፡33-34)

ከመሞቱ በፊት ሊደርስበት ያለውን በመስቀል ላይ የመቸንከሩን ሥቃይ ሲያውጠነጥነው በጸሎቱ ቃትቷል። ምንም እንኳ ሊሆን ያለውን ነገር ባይጓጓለትም፥ የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም ግን ታዝዞ ነበር።

«ደግሞ ሁለተኛ ሄዶ ጸለየና፡- አባቴ፥ ይህች ጽዋ ሳልጠጣት ታልፍ ዘንድ የማይቻል እንደሆነ፥ ፈቃድህ ትሁን አለ»

(ማቴዎስ 26፡42)

እርሱንም ለማሠር የፈለገው ፈሪሀ-እግዚአብሔር የራቀው ቡድን ሳይሆን፥ እንዲያውም ከፍተኛው የሃይማኖት ባለሥልጣን ነበር። በዚህም ጊዜ ከተባባሪዎቹ አንዱ ጥቃቱን ለመከላከልና ለመፋለም ሰይፉን መዘዟል። ኢየሱስ ግን፡-

«ወይስ አባቴን እንድለምን፥ እርሱም አሁን ከአሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክትን እንዲሰድልኝ የማይቻል ይመስልሃልን? እንዲህ ከሆነስ፡- እንደዚህ ሊሆን ይገባል የሚሉ መጻሕፍት እንዴት ይፈጸማሉ? »

(ማቴዎስ 26፡53-54)

የኢየሱስ ስቅለትና ሞት የእግዚአብሔርን ማንነት ለመገመት እና ሊያደርግ ወይንም ሊሆን የሚችለውን ወይም የማይችለውን ለመወሰንና መሆን የሚችልበትንም ሁኔታ ለመገንዘብ እንደተደረገ የሰው ጥረት ሊታይ ይችላል።

«አይሁድም ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ። ኢየሱስ፡- ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳየኋችሁ፤ ከእነርሱ ስለ ማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ? ብሎ መለሰላቸው። አይሁድም፡- ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፥ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት»

(ዮሐንስ 10፡31-33)

በሕይወቱ እጅግ ቀውጢ ሁኔታ በገጠመው ጊዜ እንኳ፥ ኢየሱስ ስለ ራሱ ሳይሆን፥ ስለ ሌሎች ነበር የገደደው።

«ቀራንዮም ወደሚባል ሥፍራ በደረሱ ጊዜ፥ በዚያ እርሱንም ክፉ አድራጊዎቹንም አንዱን በቀኝ ሁለተኛውንም በግራ ሰቀሉ። ኢየሱስም፡- አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ»

(ሉቃስ 23፡33-34)

ከትንሣኤውም በኋላ ወዳጆቹ ከጥቂቶቹ ጋር ተገናኘ፤ ይሁን እንጂ አልተገለጸላቸውም ነበር። ሊከሰትላቸው ካልቻለው ከርሱ ሞት የተነሣ እጅግ አዝነው ወደ ቤታቸው ይመለሱ ጀመር። ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው፡-

«እናንተ የማታስተውሉ፥ ነቢያትም የተናገሩትን ልባችሁ ከማመን የዘገየ፥ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ የለምን? ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጎመላቸው»

(ሉቃስ 24፡25-27)

ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት መልእክቶች ፍጻሜ በተደጋጋሚ እናነባለን። ይህ ማለት በተውራት፥ በዛቡርና በነቢያት እርሱን በተመለከተ የተተነበዩት በርካታ ትንቢቶች ከፍጻሜ መድረስ ነበረባቸው ማለት ነው። ኢየሱስ እራሱን ስቶ ነበር እንጂ በእርግጥ አልሞተም ብለው የሚናገሩ ሰዎች አሉ። ለዚህ የርሱ ምላሽ ምንድነው? «ፊተኛውና መጨረሻው፥ ሕያውም እኔ ነኝ፤ ሞቼም ነበርሁ፤ እነሆም፥ ከዘላለም እስከዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፤ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ» (ራእይ 1፡17-18)። (ሲኦል እስከ ፍርድ ቀን ድረስ የሞቱ ሰዎች የሚሰነብቱበት ሥፍራ ነው)

1. ኢየሱስ ለአይሁዶች ብቻ አልመጣም ነበርና፡-

2. እርሱ ራሱ እንዲህ ብሎአቸዋል፡-

«ክርስቶስ መከራ ይቀበላል፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፤ በስሙም ንስሓና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል»

(ሉቃስ 24፡46-47)

(«ተብሎ ተጽፎአል...» የሚለው በተውራት ውስጥ መሆኑ ነው)።

ከትንሣኤው ከ39 ቀናት በኋላ ደቀመዛሙርቱ በዓይናቸው እያዩት ኢየሱስ ወደ ሰማይ ዐረገ። ከዚያ ትንሽ ቀደም ብሎ ግን የመጨረሻ ግልጽ ትእዛዝ ሰጣቸው:-

> «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጋቸው፤ እነሆም፥ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴዎስ 28፡18-20)።

ለዚህ ነው አሁንም ክርስቲያን የሆኑ አማኞች እርሱን ከማያውቁት ጋር ለማስተዋወቅ የሚሯሯጡት። ይህም በትእዛዝ የተደረገ ከመሆኑም በላይ፥ ወደ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር መኖሪያ የመግባታችንን የመጨረሻ እውነት ያካትታል።

> «አብ ሙታንን እንደሚያነሣ፥ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው፥ እንዲሁም ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል። ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፥ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም። ወልድን የማያከብር የላከውንም አብን አያከብርም። እውነት፥ እውነት እላችኋለሁ፤ ቃሌን የሚሰማ፥ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።
>
> እውነት፥ እውነት እላችኋለሁ፤ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ እርሱም አሁን ነው፤ የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ። አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው፥ እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና። በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል»
> (ዮሐንስ 5፡21-28)

እስካሁን አንድም ነገር እንድናስብና እንድናሰላስል ሊገፋፋን ካልቻለ-ይህ መቻል አለበት! ዳሩ ግን ይህን ስጦታ በአንዳች ፍርሃት ሳቢያ ወደጎን መተው አስከፊ ጉዳይ ነው።

> «ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፤ በእኔ ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ሥፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ሄጄም ሥፍራ ባዘጋጀሁላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ፤ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ»
> (ዮሐንስ 14፡1-3)ቱ

ኢየሱስ ደግሞ ተመልሶ ይመጣል። የሚመጣውም የስርየት ስጦታውን ባልተቀበሉት ላይ ሊፈርድና የተቀበሉትን ደግሞ ቤቱ ሊወስድ ነው።

> «እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፤ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና» (ሉቃስ 12፡40)።

በተጨማሪም የምጽአቱ ሁኔታ እንዴት እንደሚሆን ገልጾልናል:-

> «የሰው ልጅም በኃይሉ ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ» (ማርቆስ 14፡62)።

> «መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ፥ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና» ማቴዎስ 24፡27።

ኢየሱስ በዓለም ማለትም በእኛ ላይ ሊፈርድ ይመጣል። ግን ምናልባት ከመምጣቱ ቀደም ብለን እንሞት ይሆናል። በዚህ ጊዜ በሞት አማካኝነት በግል ወደ እኛ ይመጣል ማለት ነው።

እዚህ ላይ ኢየሱስ ስለ ራሱ ሲናገር የእግዚአብሔር ልጅ እያለ ሳይሆን፥ የሰው ልጅ እያለ የሚጠራው ለምድነው? «የሰው ልጅ» የሚለው ስያሜ በ555 ዓ.ዓ. በተውራት ውስጥ የተወሰነ ትርጉም ተሰጥቶታል።

> «በሌሊት ራእይ አየሁ፤ እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ። በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ፤ ወደፊቱም አቀረቡት። ወገኖችና አሕዛብ፥ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብረ መንግሥትም ተሰጠው። ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፤ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው»
>
> (ዳንኤል 7፡13-14)

ይህም «የሰው ልጅ» የሚል ስያሜውን «የእግዚአብሔር ልጅ» ከሚለው ጋር ያስተካክለዋል።

በሩ ገና አልተቆለፈም። እርሱ አሁንም በመጠባበቅ ላይ ይገኛል። ታዲያ ስለምን ይህን የመጨረሻ ግብዣ አትቀበልም?

> «እነሆ፥ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ፥ ደጄንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ»
>
> (ራእይ 3፡20)

# የነቢ ዒሳ ትምህርቶች

ስለ ኢየሱስ መልእክት በመለኮታዊ ምሪት የተዘገበው ነገር በይበልጥ ያተኮረው በሥነ-ምግባር ጉዳዮች (ጽድቅ) እና በመንፈሳዊ እውነቶች ላይ ነው። ጽድቅ በሌላቸው ሰዎች ላይ የሚደርሰውን የእግዚአብሔርን ፍርድና እንዲሁም ከጽድቅ የራቀውን ሰው ከራሱ ጋር የማስታረቅ መንገዱን ነው። ኢየሱስ በሚያስተምርበት ጊዜ መልእክቱን ለማጠናከር ባመዛኙ ምሳሌዎችንና ሥዕላዊ አገላለጾችን ይጠቀም ነበር። ከእነዚህ እስቲ ጥቂቶቹን እንመልከት፡-

«በምሳሌም ብዙ ነገራቸው፤ እንዲህም አላቸው፡- እነሆ፥ ዘሪ ሊዘራ ወጣ። እርሱም ሲዘራ አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ፤ ወፎችም መጥተው በሉት። ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀ፤ ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፤ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፤ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ። ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፤ እሾህም ወጣና አነቀው። ሌላውም በመልካም መሬት ወደቀ፤ አንዱም መቶ፥ አንዱም ስድሳ፥ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።

«እንግዲህ እናንተ የዘሪውን ምሳሌ ስሙ። የመንግሥትን ቃል ሰምቶ ለማያስተውል ሁሉ፥ ክፉው ይመጣል፤ በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል፤ በመንገድ ዳር የተዘራው ይህ ነው። በጭንጫ ላይ የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ ወዲያው በደስታ የሚቀበለው ነው፤ ነገር ግን ለጊዜው ነው እንጂ በእርሱ ሥር የለውም፤ በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይሰናከላል። በእሾህ መካከል የተዘራውም ይህ ቃሉን የሚሰማ ነው፤ የዚህም ዓለም አሳብና የባለጠግነት መታለል ቃሉን ያንቃል፤ የማያፈራም ይሆናል። በመልካም መሬት የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውል ነው፤ እርሱም ፍሬ ያፈራል፤ አንዱም መቶ፥ አንዱም ስድሳ፥ አንዱም ሠላሳ ያደርጋል»

(ማቴዎስ 13፡3-9፤ 18፡23)

የሰሚዎቹን በአራት ክፍል መከፈል ለማጠናከር ኢየሱስ ሲያብራራ፡-

«መስማት ትሰማላችሁና አታስተውሉም፤ ማየትም ታያላችሁና አትመለከቱም። በዓይናቸው እንዳያዩ፥ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ፥ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፥ ተመልሰውም እንዳልፈውሳቸው የዚህ ሕዝብ ልብ ደንድኖአልና፥ ጆሮአቸውም ደንቁሮአል፤ ዓይናቸውንም ጨፍነዋል»

(ማቴዎስ 13፡14-15)

እግዚአብሔር የነቀፈው ሥጋዊውን የመስማት ብቃት ማነስ ሳይሆን፥ የሰዎችን ለመስማት አለመፈለግ ነው። ከዚህም የተነሣ ኢየሱስ የሚከተለውን ማበረታቻ ሰጥቷል፡-

«እንግዲህ እንዴት እንድትሰሙ ተጠበቁ»

(ሉቃስ 8፡18)

እንዲሁም በሌላ ምሳሌ ሌላ አስፈላጊ እውነት ገልጿል:-

«ለአንድ ሰው በወይኑ አትክልት የተተከለች በለስ ነበረችው፤ ፍሬም ሊፈልግባት መጥቶ ምንም አላገኘም። የወይን አትክልት ሠራተኛውንም:- እነሆ፥ ከዚህች በለስ ፍሬ ልፈልግ ሦስት ዓመት እየመጣሁ፥ ምንም አላገኘሁም። ቁረጣት! ስለምን ደግሞ መሬቱን ታጎሳቍላለች? አለው። እርሱ ግን መልሶ:- ጌታ ሆይ:- ዙሪያዋን እስክኰተኵትላትና ፋንድያ እስካፈስላት ድረስ በዚህች ዓመት ደግሞ ተዋት። ወደፊትም ብታፈራ ደኅና ነው፤ ያለዚያ ግን ትቆርጣታለህ አለው»

(ሉቃስ 13፡6-9)

የምናፈራው ምን ዓይነት ፍሬ ነው? ለነገሩ እኛ እኮ የፍሬ ዛፎች አይደለንም። በተጨማሪም ይህ ፍሬ ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃትና ራስን መግዛት የሚጠቃለልበት እንደሆነ ከወንጌል እንረዳለን (ገላትያ 5፡23)። እንዲህ ያለ ፍሬ ሊያሳይ የማይፈልግ ማን አለ? ሌላው የኢየሱስ ምሳሌ ይህን ግልጽ ያደርገዋል:-

«እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤ ገበሬውም አባቴ ነው። ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል፤ ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል። እናንተ ስለነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሓን ናችሁ፤ በእኔ ኑሩ፤ እኔም በእናንተ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር፥ ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፥ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም። እኔ የወይን ግንድ ነኝ፤ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና፥ በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል። በእኔ የማይኖር ቢሆን፥ እንደ ቅርንጫፍ ወደ ውጭ ይጣላል፤ ይደርቅማል፤ እነርሱንም ሰብስበው ወደ እሳት ይጥሉአቸዋል፤ ያቃጥሉአቸውማል። በእኔ ብትኖሩ፥ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ፥ የምትወዱትን ለምኑ፤ ይሆንላችሁማል። ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከበራል። አብ እንደ ወደደኝ፥ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ። እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደጠበቅሁ፥ ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ። ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን ነግሬአችኋለሁ።

«እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት። ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም። እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ፥ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ። ከእንግዲህ ወዲህ ባሮቼ አልላችሁም፤ ባርያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፤ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፤ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄአችኋለሁና። እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ፥ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ። እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ይህን አዛችኋለሁ»

(ዮሐንስ 15፡1-17)

ማንኛችንም ብንሆን በራሳችን ጥረት እንዲህ ያለውን ፍሬ ልናፈራ አንችልም። ታዲያ ይህ የሚሆነው በምንድነው? በሌላው ምሳሌ ኢየሱስ ይህንን ልብን በሚነካ መንገድ ገልጾታል፡-

> «እንዲህም አለ፡- አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት። ከእነርሱም ታናሹ አባቱን፡- አባቴ ሆይ፥ ከገንዘብህ የሚደርሰኝን ክፍል ስጠኝ አለው። ገንዘቡንም አካፈላቸው። ከጥቂት ቀንም በኋላ ታናሹ ልጅ ገንዘቡን ሁሉ ሰብስቦ ወደ ሩቅ አገር ሄደ፤ ከዚያም እያባከነ ገንዘቡን በተነ። ሁሉንም ከከሰረ በኋላ በዚያች አገር ጽኑ ራብ ሆነ፤ እርሱም ይጨነቅ ጀመር። ሄዶም ከዚያች አገር ሰዎች ከአንዱ ጋር ተዳበለ፤ እርሱም እሪያ ሊያሰማራ ወደ ሜዳ ሰደደው። እሪያዎቹም ከሚበሉት አሰር ሊጠግብ ይመኝ ነበር፤ የሚሰጠውም አልነበረም። ወደ ልቡም ተመልሶ እንዲህ አለ፡- እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ ሞያተኞች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በራብ እጠፋለሁ። ተነሥቼም ወደ አባቴ እሄዳለሁና፡- አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፤ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም፤ ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ እለዋለሁ። ተነሥቶም ወደ አባቱ መጣ። እርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት፤ ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው። ልጁም፡- አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፤ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም አለው። አባቱ ግን ባሪያዎቹን አለ፡- ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጡና አልብሱት ለእጁ ቀለበት፥ ለእግሩም ጫማ ስጡ፤ የሰባውንም ፍሪዳ አምጥታችሁ እረዱት፤ እንብላም፤ ደስም ይበለን፤ ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል፤ ጠፍቶም ነበር፤ ተገኝቶአልም። ደስም ይላቸው ጀመር»
>
> (ሉቃስ 15፡11-24)

እንደ ኮብላዩ ልጅ ሁሉ፥ እኛም «ወደ ልባችን ልንመለስ» ያስፈልገናል። ለበደሉ ምንም ማካካሻ ለማድረግ አልሞከረም። ወደ ቤት ለመሄድ ብቻ ናፈቀ - ሄደም። «ከሁሉ የተሻለው ልብስ» የኃጢአትን መሸፈን የሚያመለክት ምሳሌ ነው። እንዲሁም ቀለበቱ እንደገና በልጅነት ማዕረግ ከቤተሰቡ ለመቀላቀል ተቀባይነት ማግኘቱን ያሳያል። በተጨማሪም ባሪያዎች በዘመኑ በባዶ እግራቸው ይሄዱ ስለነበር፥ የተሰጠው ጫማ አሁን ነፃ ሰው እንደሆነ ያመለክታል። ከዚህ የምናገኘው ትምህርት በሌላው ምሳሌ ከቀረበው ጋር አንድ ዓይነት ነው፡-

> «ለአንድ አበዳሪ ሁለት ተበዳሪዎች ነበሩት፤ በአንዱ አምስት መቶ ዲናር ነበረበት፤ በሁለተኛውም አምሳ። የሚከፍሉትም ቢያጡ ለሁለቱም ተወላቸው። እንግዲህ ከእነርሱ አብልጦ የሚወደው ማንኛው ነው?»
>
> (ሉቃስ 7፡41-42)

ይቅርታ ከልባቸው ለሚጠይቁትና ከዚያም በመንገዱ ላይ በመጓዝ በእምነት ለሚከተሉት እግዚአብሔር የሚሰጠው ስጦታ ነው።

ይህ የርኅራኄ ታሪክ ከዚህ እንደሚከተለው ተደጋግሞ ተነግሮአል፡-

«ይህንም ምሳሌ ነገራቸው እንዲህ ሲል:- መቶ በግ ያለው ከእነርሱም አንዱ ቢጠፋ፥ ዘጠና ዘጠኙን በበረሃ ትቶ የጠፋውን እስኪያገኘው ድረስ ሊፈልገው የማይሄድ ከእናንተ ማነው? ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት በጫንቃው ይሸከመዋል፤ ወደ ቤቱም በመጣ ጊዜ ወዳጆቹንና ጎረቤቶቹን በአንድነት ጠርቶ:- የጠፋውን በጌን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ ይላቸዋል። እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል»

(ሉቃስ 15፡3-7)ቱ

ብዙዎቻችን እግዚአብሔር በዚህ መንገድ ይሠራል ብለን እንደማንጠብቅ እርግጠኛ ነኝ። ከእኛ የሚፈልገው ነገር ቢኖር ልባችንና ነፍሳችን እንጂ ማካካሻችንን አይደለም። «ከተበደሩት» ሰዎች ማናቸውም መልሰው ሊከፍሉ እንዳልቻሉ አስተውል። አንድ ጊዜ የተፈጸመ ኃጢአት በእኛ ጥረት ሊወገድ አይችልም። ይህ ስለ እግዚአብሔር ቅድስና፥ ስለ እኛ ኃጢአትና በሁለቱም መካከል ሊሻገሩት የማይሞከር ሠፊ ልዩነት እንዳለ ካለመረዳት ከሚመነጩት ግዙፍ ስሕተቶች አንዱ ነው። እኛ እግዚአብሔር በሚያደርግልን ነገር ላይ ሙሉ ለሙሉ ጥገኞች ነን። ይህንን ነጥብ ለማብራራት አንድ የመጨረሻ ምሳሌ እንጠቀማለን:-

«ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ ወደ መቅደስ ወጡ፤ አንዱ ፈሪሳዊ፥ ሁለተኛውም ቀራጭ። ፈሪሳዊው ቆሞ በልቡ ይህን ሲጸልይ:- እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደ ሌላ ሰው ሁሉ፥ ቀማኞችና ዓመፀኞች፥ አመንዝሮችም፥ ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ አመሰግንሃለሁ፤ በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማለሁ፥ ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወጣለሁ አለ። ቀራጩ ግን በሩቅ ቆሞ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ሊያነሣ እንኳ አልወደደም፤ ነገር ግን:- አምላክ ሆይ፥ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ እያለ ደረቱን ይደቃ ነበር። እላችኋለሁ፥ ከዚያ ይልቅ ይህ ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፥ ራሱን ግን የሚያዋርድ ከፍ ይላል»

(ሉቃስ 18፡10-14)

በዘመኑ ማኅበረሰብ ውስጥ አንድ ፈሪሳዊ በጣም የተከበረ የሃይማኖት መሪ ሲሆን፥ ከእግዚአብሔር ሕጎች ውስጥ አንዷን እንኳ ላለመተላለፍ ሲል ኑሮውን በአክራሪነትና እራሱን በመግዛት የሚመራ ነው። ጻሩ ግን በገዛ መታለሉ በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ለማጽደቅ ፈለገ። በጾሙ፥ በጸሎቱ፥ ወዘተ. ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንደሚያገኝ መስሎት ነበር። ኢየሱስ በተመሳሳይ ክፍል በግልጽ እንዲህ ብሏል:-

«የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ:- «የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፤ ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ»

(ሉቃስ 17፡10)

ይህን ልብ ልንለው ያሻል:- ትክክል ወይም ጥሩ ሥራ በመሥራት የሚያስመሰግነን ነገር አይደለም። ይህ ልንወጣው የሚገባን ኃላፊነታችን ነው።

ይልቁንም ለውድቀት የሚሰጠው ይቅርታ ሁልጊዜም ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ነው፤ የመልካም ተግባራችን ውጤት ሳይሆን፥ የርኅራኄው ሥራ ነው።

«ራሳችሁን በሰው ፊት የምታጸድቁ እናንተ ናችሁ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ልባችሁን ያውቃል፤ በሰው ዘንድ የከበረ በእግዚአብሔር ፊት ርኩሰት ነውና»
(ሉቃስ 16፡15)

ኢየሱስ አንድ ጊዜ ከሁሉ ስለሚበልጠው የእግዚአብሔር ትእዛዝ ተጠይቆ የሚከተለውን መልስ ሰጥቷል፡-

«ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹም ነፍስህም፥ በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛዪቱም ይህችን ትመስላለች፤ እርስዋም፡- ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የምትለው ናት። በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል»
(ማቴዎስ 22፡37-40)

በፍቅር ሲጠቀሙበት «መታዘዝ» የተባለው ከባድ ቃል፥ ቀላልና ግልጽ ይሆናል። ኢየሱስ ጌታ እግዚአብሔርን እንድንወድና እንድንፈራ እንዳስተማረን፥ እንዲሁ ሰዎች የሚሉትን ወይም በእኛ ላይ የሚፈጽሙትን ነገር መፍራት እንደሌለብን ነግሮናል፡-

«ሥጋን የሚገድሉትን፥ ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ»
(ማቴዎስ 10፡28)

«እኔ እላችኋለሁ፤ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል»
(ማቴዎስ 12፡36)

በእርሱና እርሱም በሚለን ነገር ብንታመን፥ እናከብረዋለን፤ ደግሞም ከእርሱ ጋር ዕርቅ አድርገናል ማለት ነው።

«እናንተ ስለወደዳችሁኝ ከእግዚአብሔርም ዘንድ እንደወጣሁ ስላመናችሁ አብ እርሱ ራሱ ይወዳችኋልና»
(ዮሐንስ 16፡27)

«የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ፤ እኔም ባለሁበት አገልጋዬ ደግሞ በዚያ ይሆናል፤ የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል»
(ዮሐንስ 12፡26)

እዚህ ላይ እውነት ሆኖ ሳለ ዘወትር የተሳሳተ አመለካከት የሚገጥመው የኢየሱስ መለኮትነት ግልጽ ሆኖ ይወጣል። ኢየሱስ ራሱም እንዲህ ብሏል፡-

«በእኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ ነው እንጂ በእኔ አይደለም፤ እኔንም የሚያይ

የላከኝን ያያል። በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር፥ እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ»

(ዮሐንስ 12፡44-46)

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ፥ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና»

(ዮሐንስ 3፡16-17)

«ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ»

(ዮሐንስ 6፡40)

«ለሚጠፋ መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ፤ እርሱን እግዚአብሔር አብ አትሞታልና»

(ዮሐንስ 6፡27)

«የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ»

(ዮሐንስ 6፡44)

«ኵላሊትንና ልብን የምመረምር እኔ እንደሆንሁ ያውቃሉ፤ ለእያንዳንዳችሁም እንደሥራችሁ እሰጣችኋለሁ»

(ዮሐንስ ራእይ 2፡23)

ኢየሱስን መከተል የሚያስከትለው ሰበብ አለ፡- ምናልባት ሊሳቅብን መሳለቅያ ልንሆን ወይንም ስደትም እንኳ ሊገጥመን ይችላል።

«በሁሉም ስለስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤ እስከመጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል»

(ማቴዎስ 10፡22)

«ባርያ ከጌታው አይበልጥም ብዬ የነገርኋችሁን ቃል አስቡ። እኔን አሳድደውኝ እንደሆኑ እናንተን ደግሞ ያሳድዱአችኋል»

(ዮሐንስ 15፡20)

ኢየሱስ ግን እንዲህ ሲል ያበረታታናል፡-

«ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ፥ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፤ ሐሤትም አድርጉ»

(ማቴዎስ 5፡11-12)

ኢየሱስ እርሱን እንድንወደው፥ እንድናከብረውና ከፍ እንድናደርገው ይፈልጋል፦

> «ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም»
> (ማቴዎስ 10፡37)

ከእግዚአብሔር ጋር ለምናደርገው እርምጃ አንዳችን ለሌላው ስለምናስፈልግ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፦

> «እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ»
> (ዮሐንስ 13፡34)

ራሳችንን ለመገምገም የምንችልበትንም አንድ መከራ ሰጥቶናል፦

> «ትእዛዜ በርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝም አባቴ ይወደዋል፤ እኔም እወደዋለሁ፤ ራሴንም እገልጥለታለሁ»
> (ዮሐንስ 14፡21)

እርሱ በንጉሥነት በታወቀበት፥ በእግዚአብሔር መንግሥት ያለው ታላቅነት ከምድራዊዎቹ ሁኔታዎች የተለየ ነው፦

> «የአሕዛብ አለቆች እንዲገዙአቸው፥ ታላላቆቹም በላያቸው እንዲሰለጥኑ ታውቃላችሁ፤ በእናንተስ እንዲህ አይደለም። ነገር ግን ከእናንተ ማንም ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፤ ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን»
> (ማቴዎስ 20፡25-27)

ውጫዊ የሃይማኖት ደንቦችንም እንደዚሁ አጋልጧል እርማትንም ሰጥቷቸዋል፦

> «ደግሞም ሕዝቡን ጠርቶ፦ ሁላችሁ እኔን ስሙ፤ አስተውሉም። ከሰው የሚወጡት ሰውን የሚያረክሱ ናቸው እንጂ፥ ከሰው ውጭ የሚገባውስ ሊያረክሰው የሚችል ምንም የለም። እናንተ ደግሞ እንደዚህ የማታስተውሉ ናችሁን? ከውጭ ወደ ሰው የሚገባ ሊያረክሰው ምንም እንዳይችል አትመለከቱምን? ወደ ሆድ ገብቶ ወደ እዳሪ ይወጣል እንጂ ወደ ልብ አይገባምና መብልን ሁሉ እያጠራ አላቸው። እርሱም አለ፦ ከሰው የሚወጣው ሰውን የሚያረክስ ይህ ነው። ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ መጎምጀት፥ ክፋት፥ ተንኰል፥ መዳራት፥ ምቀኝነት፥ ስድብ፥ ትዕቢት፥ስንፍና ናቸውና፤ ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል፤ ሰውንም ያረክሰዋል»
> (ማርቆስ 7፡14-15፤ 18-23)

ለዚህ ነው ኢየሱስ የሃይማኖት መሪዎችን የገሠጻቸው፦

«እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፡- በውስጡ ቅሚያና ስስት ሞልቶ ሳለ፥ የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ ስለምታጠሩ፥ ወዮላችሁ»

(ማቴዎስ 23፡25)

በታወቀው የ «ተራራ ላይ ስብከቱ» ከዚህ በግልጽ በተቃረነ መንገድ ኢየሱስ የሚከተለውን አስተምሯል፡-

«ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፤ እግዚአብሔርን ያዩታልና»

(ማቴዎስ 5፡8)

በዚህ ስብከቱ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት እና ሰብአዊ ግንኙነቶችን በተመለከተ በርካታ ጉዳዮችን ያነሣል። እስቲ እነዚህ ቃሎቹ ልባችንንና አዕምሮአችንን ያነቃቁት፡-

እውነተኛነትን በተመለከተ

«ደግሞ ለቀደሙት፡- በውሸት አትማል፤ ነገር ግን መሐላዎችህን ለጌታ ስጥ» እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፡- «ከቶ አትማሉ፤ ነገር ግን ቃላችሁ ‹አዎን› ‹አዎን› ወይም ‹አይደለም› ‹አይደለም› ይሁን፤ ከእነዚህም የወጣ ከክፉው ነው»

(ማቴዎስ 5፡33-34፥ 37)

ሌሎችን ስለ መውደድ፡-

«ባልንጀራህን ውደድ፤ ጠላትህንም ጥላ» እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፤ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፤ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፤ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፤ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና። የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ»

(ማቴዎስ 5፡43-48)

ስለ ሃይማኖታዊ ሥነ ምግባርና ስለ ጸሎት

«ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤ ያለዚያ በሰማያት ባለ አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም።

«እንግዲህ ምጽዋት ስታደርግ፥ ግብዞች በሰው ዘንድ ሊከበሩ በምኩራብ፥ በመንገድም እንደሚያደርጉ መለከት በፊትህ አታስነፋ፤ እውነት እላችኋለሁ፤ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ፥ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል።

«አሕዛብም በመናገራቸው ብዛት እንዲሰሙ ይመስላቸዋልና፥ ስትጸልዩ እንደ እነርሱ በከንቱ አትድገሙ። ስለዚህ አትምሰሉአቸው፤ ሳትለምኑት አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና። እንግዲህ፥ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፡- ‹በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፥ ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤ የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤ እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል፥ በደላችንን ይቅር በለን፤ ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን፤ መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ አሜን›። ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ፥ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና፤ ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ፥ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም»

(ማቴዎስ 6፡ 1-15)

## በይቅርታና በጸሎት መሐከል ያለው ዝምድና

«ለጸሎትም በቆማችሁ ጊዜ፥ በሰማያት ያለው አባታችሁ ደግሞ ይቅር እንዲላችሁ፥ በማንም ላይ አንዳች ቢኖርባችሁ ይቅር በሉት»

(ማርቆስ 11፡ 25)

## ስለ ጾም

«ስትጦሙም፥ እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፤ ለሰዎች እንደ ጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፉሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፤ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ስትጦም፥ በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደ ጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ፤ ፊትህንም ታጠብ፤ በስውር የሚያይ አባትህ በግልጥ ይከፍልሃል።»

«ብልና ዝገትም በሚያጠፉት፥ ሌቦችም ቆፍረው በሚሰርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፤ ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት፥ ሌቦችም ቆፍረው በማይሰርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፤ መዝገብህ ባለበት ልብህ በዚያ ይሆናልና»

(ማቴዎስ 6፡ 16-21)

## ስለ ቁሳቁሳዊ (ዓለምን መውደድ)

«ከሁሉ በሚያንስ የታመነ፥ በብዙ ደግሞ የታመነ ነው፤ ከሁሉ በሚያንስም የሚያምፅ፥ በብዙ ደግሞ ዓመፀኛ ነው። እንግዲህ በዓመፃ ገንዘብ ካልታመናችሁ፥ እውነተኛውን ገንዘብ ማን ይሰጣችኋል? ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ባሪያ ማንም የለም። ወይም አንዱን ይጠላልና ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋልና፥ ሁለተኛውንም ይንቃል። ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም»

(ሉቃስ 16፡ 10-13)

## ስለ ጭንቀትና ኀዘን

«ስለዚህ እላችኋለሁ፤ ስለ ነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት፥ ወይም ስለ ሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ፤ ነፍስ ከመብል፥ ሰውነቱም ከልብስ

አይበልጥምን? ወደሰማይ ወፎች ተመልከቱ፤ አይዘሩም፤ አያጭዱምም፤ በጎተራም አይከቱም፤ የሰማዩ አባታችሁም ይመግባቸዋል፤ እናንተ ከእነርሱ እጅግ አትበልጡምን? ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማነው? ስለ ልብስስ ስለምን ትጨነቃላችሁ? የሜዳ አበቦች እንዴት እንዲያድጉ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ፤ አይደክሙም፤ አይፈትሉምም፤ ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ሰለሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከነዚህ እንደ አንዱ አልለበሰም። እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን የሜዳን ሣር እንዲህ የሚያለብሰው ከሆነ፥ እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ እናንተንማ ይልቁን እንዴት? እንግዲህ፦ ‹ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን?› ብላችሁ አትጨነቁ፤ ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና። ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት፥ ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።

«ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል»
(ማቴዎስ 6፡25-34)

## በሌሎች ላይ ስለ መፍረድ

«እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ፤ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋልና በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፍርባችኋል። በወንድምህም ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ? በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለምን አትመለከትም? ወይም ወንድምህን፦ «ከዓይንህ ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ» እንዴትስ ትለዋለህ? እነሆም፥ በዓይንህ ምሰሶ አለ። አንተ ግብዝ፥ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ፤ ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ጉድፉን ለማውጣት አጥርተህ ታያለህ»
(ማቴዎስ 7፡1-5)

## ወሳኙ ነጥብ

«በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሠፊ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና፥ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤ ወደ ሕይወትም የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው»
(ማቴዎስ 7፡13-14)

## ስለ ግብዝነት

«በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። በዚያ ቀን ብዙዎች፦ ‹ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገረንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜም፦ ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።

«ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ፤ ጎርፍም መጣ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንም ቤት

ገፋው፤ በዓለት ላይም ስለተመሠረተ አልወደቀም። ይህንም ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ፤ ጎርፍም መጣ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንም ቤት መታው፤ ወደቀም፤ አወዳደቁም ታላቅ ሆነ»

(ማቴዎስ 7፡21-27)

በዓለም ላይ አንድ ቁጥር የሆነው ችግር የግንኙነቶች መፈራረስ ነው። ኢየሱስ ከራሱ ቃል አንጻር ሲታይ የመጣው በመጀመሪያ ደረጃ ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቀን አስፈልጎታል፤ ምክንያቱም ሁላችንም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረን ግንኙነት በመበላሸቱ እየተሰቃየን ነበር። እንዲሁም የተበላሸውን የሰዎች የርስበርስ ግንኙነትንም ለመፈወስ መጥቷል። በተለይ በጋብቻ የተጣመሩትን ሰዎች የታማኝነትን ጉድለት በተመለከተ እንዲህ ብሏቸዋል፡-

«አታመንዝር እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል»

(ማቴዎስ 5፡27-28)

የዚህ ኃጢአት እውነተኛ አደገኛነት ለመግለጽ ኢየሱስ በጣም አስደንጋጭ የሆነ ሥዕላዊ መግለጫ ሲጠቀም እንመለከታለን፡-

«ቀኝ ዓይንህ ብታሰናክልህ፥ አውጥተህ ከአንተ ጣላት፤ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻልሃልና። ቀኝ እጅህም ብታሰናክልህ ቆርጠህ ከአንተ ጣላት፤ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻላልና»

(ማቴዎስ 5፡29-30)

ኢየሱስ ሁለት አንድ ዓይነት የሆኑ ቃላትን ሁለት ጊዜ በመደጋገም የጠቀሰው በእርግጥ ያለበቂ ምክንያት አልነበረም። ዳሩ ግን በሐሳብም ሆነ በሥራ የሚፈጸመውን የኃጢአት አስከፊነት ለማስረገጥ ነው። ሰው መቼም መልካም መስሎ ከማይታየው ጉዳይ እራሱን የሚያሾልክበትን ቀዳዳ አያጣም። ኢየሱስ ይህን ጉዳይ ይጠቅሳል፡-

«ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፤ አለም፡- ‹ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ› የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው»

(ማቴዎስ 19፡4-6)

«ሚስቱን የሚፈታት ሁሉ የፍችዋን ጽሕፈት ይስጣት ተባለ። እኔ ግን እላችኋለሁ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፤ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል»

(ማቴዎስ 5፡31-32)

«ሚስቱንም የሚፈታ ሁሉ ሌላይቱንም የሚያገባ ያመነዝራል፤ ከባልዋም የተፋታችውን የሚያገባ ያመነዝራል»

(ሉቃስ 16፡18)

«ሙሴስ ስለ ልባችሁ ጥንካሬ ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ?። ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም። እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላዪቱን የሚያገባ ሁሉ ያመናዝራል»፤ «የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል»

(ማቴዎስ 19፡8-9)

እግዚአብሔር እጅግ ከፍ ያለ መመዘኛ ቢኖረውም ቅሉ፥ ኢየሱስ እያንዳንዳችን ይቅር እንድንባባል ይፈልጋል። እንዲያውም ይህ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታን ለመቀበል ቅድመ-ሁኔታ ነው። ኢየሱስ ለእኛ ጸሎትን ባስተማረበት በጸሎቱ ናሙና ውስጥ የሚከተለው ተጽፎአል:-

«የበደሉንን ይቅር እንደምንል፥ በደላችንን ይቅር በለን»

(ማቴዎስ 6፡12)

እንዲሁም የሚከተለውን አሳብ አክሏል:-

«ወንድምህ ቢበድልህ ገሥጸው፤ ቢጸጸትም ይቅር በለው። በቀንም ሰባት ጊዜ እንኳ ቢበድልህ በቀንም ሰባት ጊዜ:- ‹ተጸጸትሁ› እያለ ወደ አንተ ቢመለስ ይቅር በለው»

(ሉቃስ 17፡3-4)

አንደኛው የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ስንት ጊዜ ወንድሙን ይቅር ማለት እንዳለበት በመጠየቅ፥ «እስከ ሰባት ጊዜ ነውን?» አለ። ኢየሱስም የሚከተለውን መልስ ሰጥቶታል:-

«እስከ ሰባት ጊዜ ሰባ እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም»

(ማቴዎስ 18፡22)።

ስለ ኢየሱስ አንድ ልብን የሚነካ ምሳሌ ተመዝግቦአል። እርሱ ምን ያህል የይቅርታ መንፈስ እንደነበረው ለማስተላለፍ በኢየሱስ የተነገሩትን ቃላት ብቻ ሳይሆን፥ ጠቅላላውን ታሪክ መናገር ይኖርብናል:-

«ኢየሱስ ግን ወደ ደብረ ዘይት ሄደ። ማለዳም ደግሞ ወደ መቅደስ ደረሰ፤ ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ መጡ። ተቀምጦም ያስተምራቸው ነበር። ጻፎችና ፈሪሳውያንም በምንዝር የተያዘችን ሴት ወደ እርሱ አመጡ፤ በመካከልም እርስዋን አቁመው:- ‹መምህር ሆይ፥ ይህች ሴት ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች፤ ሙሴም እንደነዚህ ያሉት እንዲወገሩ በሕግ አዘዘን፤ አንተስ ስለ እርስዋ ምን ትላለህ?› አሉት። የሚከሱበትንም እንዲያገኙ ሊፈትኑት ይህን አሉ። ኢየሱስ ግን ጎንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ፤ መላልሰው በጠየቁት ጊዜ ግን ቀና ብሎ:- ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት› አላቸው። ደግሞም ጎንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ። እነርሱም ይህን ሲሰሙ ኅሊናቸው ወቀሳቸውና ከሽማግሌዎች

ጀምረው እስከ ኋለኞች አንድ አንድ እያሉ ወጡ፤ ኢየሱስም ብቻውን ቀረ፤ ሴቲቱም በመካከል ቆማ ነበረች። ኢየሱስም ቀና ብሎ ከሴቲቱ በቀር ማንንም ባላየ ጊዜ፡- ‹አንቺ ሴት፥ እነዚያ ከሳሾችሽ ወዴት አሉ? የፈረደብሽ የለምን?› አላት። እርስዋም፡- ‹ጌታ ሆይ፥ አንድ ስንኳ› አለች። ኢየሱስም፡- ‹እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ፤ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ› አላት»

(ዮሐንስ 8፡1-11)

እግዚአብሔር በተፈጥሮው ኃጢአትን የማይታገሥ ሆኖ ሳለ፥ ለሚጸጸቱ ኃጢአተኞች የሚያሳየው ርኅራኄ ግን እጅግ ልብ የሚነካ ነው።

የሚያሳዝነው ግን የተጠመቀ ወይም የቤተክርስቲያን አባል የሆነ ሁሉ እውነተኛ ክርስትያን አለመሆኑ ነው፡-

«ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል፤ ከእኔ ጋርም የማያከማች ይበትናል»

(ማቴዎስ 12፡30)

«ኢየሱስም፡- ‹እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀመዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነትም አርነት ያወጣችኋል› አላቸው »

(ዮሐንስ 8፡31)

«ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፡- ‹እውነት፥ እውነት እላችኋለሁ፤ ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባርያ ነው»

(ዮሐንስ 8፡34)

ከዚህ ላይ የአንድን አማኝ ሦስት ባሕሪያት እንመለከታለን፡- እውነትን ያውቃል፤ የኢየሱስን ትምህርት ይከተላል፤ ከእርሱ ጋር ያከማቻል፤ ማለትም እውነት ስለሆነው ኢየሱስ የሚያውቀውን ለሌሎች ያካፍላል። ያም ነፃ ያወጣዋል።

እዚህ ላይ በትክክል ከተፈጥሮ የላቀ ነገር ያስፈልጋል፡-

«ኢየሱስም መልሶ፡- «እውነት እውነት እልሃለሁ፤ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም»

(ዮሐንስ 3፡3)

ኢየሱስ በመቀጠልም ካለዚህ ልምምድ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ እንደማይችል አከሏል። ይህም ለመግለጽ የሚሻው ሥጋዊ ሕይወት በሥጋዊ ልደት እንደሚጀምር ሁሉ መንፈሳዊ ሕይወትም የራሱ ጅማሬ እንዳለው ነው። በመሆኑም ዘላለማዊ ሕይወት የሚጀምረው ከመንፈሳዊ ልደት ነው። የሚጀምረውም በብርሃን ወዳለ ሕይወት «ነፃ ስንወጣ» ወይም «ስንወለድ» እና በእውነትም ከልባችን ስንመላለስ ነው። የኃጢአት ሰንሰለት ከእኛ ላይ በወለቀ ጊዜ፥ ጥፋታችንም በተወገደ ጊዜ፥ ያኔ ነፃ ወጥተናል። እንዲሁም «አዲሱ ሕይወት» ኃጢአትን እንድንጠላ፥ ጽድቅን እንድንወድና ነፃ ያወጣንን መሢሑን ኢየሱስን እንድንከተል ያስችለናል። ይህም ሁሉ የሚጀምረው ያንኑ ለማድረግ ከመወሰን፥ የእግዚአብሔርን ስጦታ

ለመቀበል ከመፈለግ፥ ይቅርታውንና ጸጋውንም ከመሻት ነው። ቃሉንና ፈቃዱን ለማጥናትና በዚያውም ለመኖር በመወሰን አእምሮህና ነፍስህ መንፈሳዊ ብርሃን እንዲበራላቸው እርሱን በመጠየቅ የሚፈጸም ነው።

## መደምደሚያ

የነቢ ዒሳ መልእክት ሙስሊሞች እንዲያምኑ ከተማሩት ጋር እንደሚጋጭ ሁላችንም እንረዳለን። በእርግጥ ኢየሱስ ከነቢይ እንደማይበልጥ፥ አምላክ ወይም የሁሉን ቻይ እግዚአብሔር አካል እንዳልሆነ (ሱረቱ 4፡41፤ 5፡75-81፥ 119፤ 9፡30፤ 19፡35)፥ እንዳልተሰቀለ ወይም እንዳልሞተ (ሱረቱ 4፡157) ከሚያስተምረው ከራሱ ከቁርዓን ጋርም ቢሆን ይጋጫል። ከዚህም የተነሣ ከኃጢአታችን አስጨናቂ ውጤት ይቅር ሊለንና ሊያድነን እንደማይችል ይናገራሉ።

ስለ ኢየሱስ እውነተኛ ማንነት ትክክለኛ መልስ፥ እርሱ ስላከናወናቸው ነገሮች፥ እንዲሁም የትኞቹ እውነትን ከመጻሕፍት እንደሚያንጸባርቁ ማወቁ የሕይወታችን ዐቢይ ጉዳይ ነው። እያንዳንዱ ሙስሊም በውስጣዊ ስሜቱ ገና ድሮ በአንድ በኩል ወስኗል፤ እያንዳንዱ ክርስቲያንም በሌላ። ይሁን እንጂ ያ እውነትን ወይም ሐቆችን ሊቀይረው የሚችል የለም።

ይህን ለመወሰን የሚያስችል አንዳች መንገድ ይኖር ይሆን? ከሌለ ስሕተትን ወይም ውሸትን በማመናችን እግዚአብሔር እስከዚህ ተጠያቂዎች ሊያደርገን አይችልም ነበር! ብዙ ሰዎች ይህን የማይረዱት ምናልባት ለማወቅ በቂ ፍላጎት ስለሌላቸውና በራሳቸውም አቋም አለመሳሳት እርግጠኞች ሆነው ስለሚገምቱ ይሆናል። እምነት በእውነትና በስሕተት መካከል ለመዳኘት አያስችልም። ተገቢውም መሣሪያ አይደለም። ጥልቅ እይታና እውቀት ስለሚያስፈልጉ፥ እነዚህን በታማኝነትና አድልዎ በሌለበት ሁኔታ መጠቀም ያሻል።

እግዚአብሔር በግልጽ እውቀትን እንደሰጠ ግልጽ ነው፥ ወይስ በተሻለ ሁኔታ እውነትን የሚያረጋግጥ መረጃ ሰጥቷል ብንል ይሻላል!

እግዚአብሔር ለሙሴ በሰጠውና (ዘዳግም 18፡21-22) ኋላም በሌሎች በርካታ ነቢያት በኩል (ኢሳይያስ 41፡21፤ አሞጽ 3፡7፤ ኤርምያስ 28፡9 ወዘተ.) በላከው መልእክቱ፥ ማንም ሊኮርጀው የማይችለውን አንድ የደራሲነቱ ምልክት አሳይቷል፦ ይህም ትንቢት ነው። ከግምት ውጪ የሆኑ ታሪካዊ ክስተቶች ከስሕተት በጠራ ሁኔታ ተተንብየዋል። የነዚህም ትንቢቶች መፈጸም መለኮታዊ ድርሰትነቱን ያረጋግጣል። ከ750 እና ከ1000 ዓመታት ወይም ከዚህም በፊት ከልደቱ አስቀድሞ ሙሴ፥ ዳዊት፥ ኢሳይያስና ሌሎችም ስለ መሢሑ ኢየሱስ መምጣትና ሕይወት ሲተነብዩ፥ እግዚአብሔር ምልክት ሰጥቷል። በሁሉም መስከ ብርቅዬ የሆኑትን እነዚህን ትንቢቶች ሁሉ ኢየሱስ በራሱ በፈጸመ ጊዜ፥ እውነቱን ለማረጋገጥ መሻቱ ላለው ሁሉ ትንቢቶቹ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጡ መሆን እንዳለባቸውና ኢየሱስም እንደተተነበየለት አማኑኤል እንደሆነ ተገለጠ። እርሱም «ከድንግል የተወለደ ሕፃን» (ኢሳይያስ 7፡14)፥ «ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ»

(ኢሳይያስ 9፡6) ነው። እርሱም «መድኃኒት የሆነላቸው» (ለበዕብራይስጥ ጄሹዋ (ኢያሱ) ለ ኢየሱስ)፥ «ያዳናቸው» እና «በፍቅሩና በርኅራኄውም የተቤዣቸው» (ኢሳይያስ 63፡7-9) እግዚአብሔር ነው።

«እነርሱ ግን ዓመፁ፤ ቅዱስ መንፈሱንም አስመረሩ» (ቁ. 10)

ይህም ዓመፅ ኢየሱስን በመቃወምና በመግደል አከተሚል፡-

«የተናቀ፥ ከሰውም የተጠላ፥ የሕመም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው፤ ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው፤ እኛም አላከበርነውም።

«በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕመማችንንም ተሸክሞአል፤ እኛ ግን እንደተመታ በእግዚአብሔርም እንደተቀሠፈ፥ እንደተቸገረም ቆጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፤ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደበጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛም እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።

«ተጨነቀ፤ ተሠቃየም፤ አፉንም አልከፈተም፤ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፥ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፤ ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ፤ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ፤ ሆኖም ግፍን አላደረገም ነበር፤ በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም ነበር።

«እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ፤ ነፍሱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል፤ ዕድሜውም ይረዝማል፤ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል። ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል፤ ደስም ይለዋል፤ ጻድቅ ባሪያዬ በዕውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፤ ኃጢአታቸውንም ይሸከማል። ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፤ ከኃያላንም ጋር ምርኮን ይካፈላል፤ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፥ ከዓመፀኞችም ጋር ተቆጥሮአልና፤ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፤ ስለ ዓመፀኞችም ማለደ»

(ኢሳይያስ 53፡3-12)

የአሟሟቱ ሁኔታም ሳይቀር ተተንብዮአል፡-

«ብዙ ውሾች ከብበውኛልና፤
የክፉተኞችም ጉባኤ ያዘኝ፤
እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ።
አጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ፤
እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም።
ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፤
በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ»

(መዝሙር (22)፡ 16-18)

ጥንቁቅ አንባቢ በዚህች አነስተኛ መጽሐፍ ውስጥ የተንጸባረቀው የነቢ ዒሳ መልእክት እውነተኛነቱን እንዲያረጋግጡልን ከተሰጡት ትንቢቶች ጋር እንዴት እንደሚስማማ ሊመለከት ይችላል።

በዚህ መልእክት ብርሃንና በመረጃዎች በበለጸገ ተአማኒነቱ እየተረዳን ከሚያስከትላቸው ውጤቶችን ሁሉ መቀበል፥ ወይስ መልእክቱንና የመልእክቱን ባለቤት ችላ ማለት እንዳለብን እያንዳንዳችን መወሰን ይኖርብናል። ችላ ስንለውም የእግዚአብሔርን የይቅርታ ስጦታ፥ ከእርሱ ጋርም መታረቅና ተቀባይነት ማግኘትን እንተዋለን። በሕጉም መሠረት ተቀባይነት ያላገኘ ይቅርታ ውጤቶቹንም ሁሉ አስከትሎ የሚሄድ ነው።

ምናልባት አሁንም በርካታ ያልተመለሱ ጥያቄዎች ይኖሩ ይሆናል። በጊዜአቸው መመለስ ያስፈልጋቸዋል፤ ይገባቸዋልም። ዳሩ ግን እነዚህ ጥያቄዎች በኢየሱስ በኩል በመስቀል ላይ ተገልጾ እኛን ከራሱ ጋር ሊያስታርቀን ከሚፈልገውና ያለእርሱም ማንም ቢሆን ወደ መንግሥተ-ሰማይ የመግባት ብቃት የማያገኘውን አንዱንና ብቸኛውን እግዚአብሔርን ላለመቀበል ምክንያት ሊሆኑን አይገባም። እንዲሁም ይህን የነቢ ዒሳን መልእክት በፍጹም አትዘንጋ፡-

> «እነሆ፥ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ፥ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ . . .»

እንዲገባ ትፈቅድለታለህ?

ጥያቄ ወይም እንዲህ ያለ መንፈሳዊ ጽሑፍ ከፈለጋችሁ

ለሕይወት በር

የመ. ሣ. ቁጥር 4937

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ በማለት ጻፉልን።